# በኢትዮጵያውያን ልጆች አስተዳደግ ላይ ያተኮረ መጽሐፍ በለንደን ተመረቀ

ኃይሉ አብርሃም ከለንደን

(habra16@yahoo.co.uk)




በአቀራረቡ እና በይዘቱ ዘመኑን ያገናዘበ ነው የተባለለት " የልጆች አስተዳደግ በዚህ ዘመን ተግዳሮቶቹ እና መፍትሔዎቹ " የተሰኘ አዲስ መጽሐፍ ግንቦት 10 2006 ዓ.ም (18 May 2014) በለንደን ተመረቀ። በዕለቱም በተለይ ከኢትዮጵያ ውጪ ያሉ ወላጆች በልጆች አስተዳደግ ዙሪያ ባሉባቸው ችግሮች ላይ በዩኬ በሚገኙ ምሁራን ሰፊ ውይይት ተካሂዷል። በዓይነቱ የመጀመሪያ የሆነው ይህ መጽሐፍ በአዲስ አበባ መምህርት በሆኑት ወ/ሮ ፈሰስ ገ/ሃና እና በዩናይትድ ኪንግደም በታዳሽ ኃይል (Renewable energy ) ተመራማሪ የሆኑት ዶ/ር በላቸው ጨከነ የተጻፈ ነው። አዘጋጆቹ ከዚህ በፊት የአማርኛ ቋንቋን እና የኢትዮጵያ እሴቶች ለልጆች ማስተማሪያ በዲቪዲ አዘጋጅተው አቅርበዋል።

የመጽሐፉን አጠቃላይ ዓላማ በተመለከተ ዶ/ር በላቸው በዕለቱ ለተገኙት ታዳሚዎች ሲገልጹ “ባለንበት ዘመን የአኗኗር ዘይቤ መቀየር፣ የኑሮ ጫና፣ የዓለም መቀራረብ በአሁኑ ወቅት የልጆችን አስተዳደግ ለሁሉም ወላጅ ለማለት በሚያስደፍር መልኩ ከባድ አድርጎታል። በተለይ ከኢትዮጵያ ውጪ ያለን ወላጆች ለሀገሩ ባህል እና ሕግ እንግዳነት፣ ከቤተ ዘመድ መራቃችን፣ የስራ ጫና፣ የግዜ እጥረት እና የዓለም ነጋዴዎች ለልጆች የሚያቀርቡት ተለዋዋጭ ሸቀጥ የልጅ አስተዳደግን የበለጠ ውስብስብ አድርጎብናል። ይህን ችግር በመረዳት በኢትዮጵያም ሆነ ከኢትዮጵያ ውጪ ያሉ ወላጆች እንደ መርጃ እንዲያገለግላቸው፣ ለልጆቻቸው የሚያደርጉትን ነገር ሁሉ በሙሉ ልብ (with self-confidence) እንዲያደርጉ እና ሳይንሳዊ መንገዶችን ከኢትዮጵያዊ ዕሴቶች ጋር በማጣመር እንዲጓዙ የልጆች አስተዳደግ በዚህ ዘመን ተግዳሮቶቹ እና መፍትሔዎቹ የሚለውን መጽሐፍ ለማዘጋጀት አሰብን።” በማለት መጽሐፉን ለማዘጋጀት ከአራት አመት በፊት እንደጀመሩት ገልጸዋል።

"የልጆች አስተዳደግ በዚህ ዘመን፤ ተግዳሮቶቹ እና መፍትሔዎቹ " መጽሐፍ በውስጥ ገጾቹ የልጅን ምንነት ከመውለድ እና ከመወለድ ባለፈ ያለውን ቁም ነገር በጥልቅ ተብራርቶበታል። በዚህ ጉዳይ ላይ ከኢትዮጵያ ውጪ ለሚኖሩ ኢትዮጵያውያን በወላጆች እና በልጆች መካከል ያለው ግንኙነት ላቅ ያለ ትርጉም እንዳለው ያስገነዝባል። በልጆች እድገት፣ የጠባይ ለውጥ እና ፍላጎት ላይ የኛ ኢትዮጵያውያን ወላጆች በልጆቻችን ጉዳይ ያለን ልማዳዊ እና ልጆቻችን በወደፊት ሕይወት ላይ ተጽእኖ የሚያሳድር ጎጂ አመለካከቶቻችንን ከሥነ ልቦና ባለሞያዎች አስተያየቶች ጋር አገናዝቦ ሰፊ ትንተና ይሰጥበታል። ከኢኮኖሚ አቅማችን፣ካደግንበት ማኅበረሰብ፣ እኛም ካለን ትክክለኛ እና ሚዛናዊ ያልሆነ በሚመስል መልኩ "ልጄ እንደ እኔ እንዲሆን አልፈልግም" ከሚል አመለካከት በመነሳት ለልጆቻችን የምናቀርብላቸው መጫወቻዎች፤ የሚያያቸው የቴሌቪዥን ፕሮግራሞች ዓይነት እና የጊዜ አጠቃቀማቸው በልጆች ላይ ያላቸውን ተጽእኖዎች በማብራራት የልጆች የመስክ እይታ፣ የገንዘብ አያያዝ፣ የትምህርት አጠናን ዘዴን እና የልጆች የሥራ ባህል ምን መምሰል እንዳለበት ይዘረዝራል።

ዶ/ር በላቸው ጨከነ በመርሐ ግብሩ ላይ መጽሐፉ ያሉትን ሌሎች ይዘቶች ሲገልጹ እንዲህ ብለዋል። “በአሁኑ ወቅት የተለመዱትን ወላጅ መር (አምባገነን)፣ አሳታፊ፣ መረን እና ቁብ የለሽ የተባሉት  የልጆች አስተዳደግ ዓይነቶችን ጠንካራ እና ደካማ ጎናቸውን ይተነትናል። በልጆች የሚፈጸሙ ጥፋቶች እና የእርምት እርምጃዎችን ከባለሞያዎች አስተያየት አንጻር ምን መምሰል እንዳለበት ያብራራል።  ውጤታማ እና ጤናማ ልጆችን ለማፍራት ባለድርሻ አካላት እነማን ናቸው ብሎ ይጠይቃል፤ በልጆች አስተዳደግ የወላጆች፣ የትምህርት ቤቶች፣ የሃይማኖት ተቋማት እና የመንግሥትን ሚና በዝርዝር ያስቀምጣል። በተለይ ከኢትዮጵያ ውጭ ያሉ ኢትዮጵያውያን እና ትውልደ ኢትዮጵያዊያን በልጅ አስተዳደግ ዙሪያ ያሉባቸውን ችግሮች፣ መንሥኤዎች እና መፍትሔዎች ይዳስሳል። በመጨረሻም በልጅ አስተዳደግ ወላጅ ያለውን በራስ የመተማመን እና ለልጅ የሚያስፈልጉትን መሠረታዊ ነገሮች እያደረገ እንደሆን ራሱን መመዘኛ ያስቀምጣል።



ፎቶ ሚሊዮን  ( ዶ/ር በላቸው ጨከነ ከአቶ ዮስያስ ታደሰ እና ከዶ/ር ብርሃኑ ተሾመ ጋር በመጽሐፋቸው ምረቃ ላይ)

የመጽሐፉ ጸሐፊዎች እነዚህን አርዕስተ ጉዳዮች በሰፊው ለመተንተን የልጆች አያያዝን በማስመልከት በመጠይቅ፣ በቃለ መጠይቅ እና በጋራ ውይይት ከሀገር ቤት እና ከባህር ማዶ ከሚገኙ ወላጆች፣ መምህራን፣ ልጆች እና ከሥነ ልቦና ባለሞያዎች መረጃዎችን በመሰብሰብ እና በርእሰ ጉዳዩ ዙሪያ የተጻፉ ልዩ ልዩ መጻሕፍትን እና ጥናቶችን በመዳሰስ እና ቀጥተኛ የሕይወት ልምዶችን ከመቀመር በተጨማሪ በመርጃ ምንጭነት ከ300 ሰው በላይ አሳትፈዋል።

በውይይት መርሐ ግብሩ ላይ ከለንደን እና በዩናይትድ ኪንግደም ካሉ ሌሎች ከተሞች በእድምተኝነት የተሳተፉ ሲሆን አቶ ዮስያስ ታደሰ የሕግ እና ቢዝነስ አማካሪ በክብር እንግድነት፣ ዶ/ር አማረ ደስታ ከሳውዝ ባንክ ዩኒቨርሲቲ፣ ወ/ሮ ብርሃኔ ዶሪ ከለንደን ሜትሮፖሊታን ዩኒቨርሲቲ ፣ ዶ/ር ብርሃኑ ተሾመ  ከስኩል ኦፍ ለንደን፣ ወ/ሮ ሃና ደምሴ በለንደን የጀርመን ድምጽ የአማርኛ ፕሮግራም ዘጋቢ፣ አቶ ቴዎድሮስ መከተ  ከኤስኤምቢሲ ባንክ በተናጋሪነት እና በአወያይነት ተሳታፊ ሆነዋል። በዶ/ር ብርሃኑ ተሾመ እና በወ/ሮ ሃና ደምሴ መርሐ ግብሩን በመምራት የተጀመረ ሲሆን የክብር እንግዳው አቶ ዮስያስ ታደሰ በኢትዮጵያ ወላጆች ዙሪያ ያሉትን ችግሮች ከቤተሰብ፣ ከማኅበረሰብ( ኮሚኒት) እና  ካለንበት ሀገር ፖሊሲ አንጻር ምን ምን እንደሆኑ በመረጃ አስደግፎ አቅርበውታል። በንግግራቸው  ማጠቃለያም ይህን መጽሐፍ በአጭሩ ግለጸው ብባል የምለው “ ሁሉም ቤተሰቦች ሊያነቡት የሚገባ በቀላል ቋንቋ ስለ ልጅ መልካም አስተዳደግ እና ተግዳሮቶች ከብዙ አንጻር የሚያስገነዝብ እና የሚያነቃቃ ማስተወሻ  "ሃንድ ቡክ ነው" እላለሁ ብለዋል።



ፎቶ ሚሊዮን ( ወ/ሮ ብርሃኔ ዶሪ፣ ዶ/ር አማረ ደስታ፣ ዶ/ር በላቸው ጨከነ፣ አቶ ቴዎድሮስ መከተ፣ ወ/ሮ ሃና ደምሴ እና ዶ/ር ብርሃኑ ተሾመ )

ወ/ሮ ብርሃኔ ዶሪ " የልጆች ባሕርያት ከጽንሰት እስከ ወጣትነት" በሚለው አርዕስት ሰፊ ማብራራያ ሰጥተዋል። ልጆች ገና ከማህጸን ጀምሮ የተለያየ እድገት የሚያሳዩ ሲሆን በእነዚህ ጊዜያት ወላጅ በየዕድሜ ክልላቸው በጥንቃቄ በመያዝ በራስ መተማመንን እንዲያጎለብቱ ማድረግ እንደሚገባ ገልጸዋል። ወላጅ ልጁን በፍቅር፣ በክትትል እና በሥርዓት ማሳደግ እንደሚገባው የንግግራቸው አንኳር መልእክት ነበር።

ቀጣዩ ተናጋሪ ዶ/ር አማረ ደስታ ምስጋናቸውን ለአዘጋጆቹ ካቀረቡ በማቅረብ “ ምን አለ ይህን መጽሐፍ ልጆቼን ከመውለዴ በፊት አግኝቼው ቢሆን ኖሮ ” በማለት ነው ንግግራቸውን የጀመሩት። በውጪ ያሉ ኢትዮጵያውያን በልጆች አስተዳደግ ዙሪያ ያሉባቸው መሠረታዊ ችግሮች በዓለም የአኗኗር ዘይቤ መቀየር፣ ኢትዮጵያዊያን ወላጆች ከቤተሰብ እና ከጎረቤት ርቀው በብቻ መኖር እና የቴክኖሎጂ ጫና ምን ያህል ችግር እየፈጠረ እንደሆን በሰፊው በምሳሌ አብራርተዋል።

የመጨረሻው ንግግር በአቶ ቴዎድሮስ መከተ ሲሆን " የዘመኑን ቴክኖሎጂ ለልጆች እንዴት እንጠቀም?" በሚሉ ርእሶች ከሙያቸው እና ከልምዳቸው አንጻር የገለጹ ሲሆን ቴክኖሎጂ ለልጆቻችን በአግባቡ መጠቀም እንደሚገባ እና ልጆችን ለመከታተል እና ለመቆጣጠር የተለያዩ መንገዶችን መጠቀም እንደሚገባ አስረግጠው ገልጸዋል።

ከገለጻው በኋላም ከእድምተኞች የተለያዩ ጥያቄዎችና አስተያየቶች ቀርበው ከተናጋሪዎቹ በቂ መልስ እና ማብራሪያ ተሰጥቶባቸዋል። ይህ ዓይነቱ ውይይት በተለያዩ ከተሞች መካሄድ እንዳለበት እና ጉዳዩ ትውልድ የማትረፍ ስራ በመሆኑ ሁሉም ባለ ድርሻ አካላት ሊሠሩበት እንደሚገባ ተሰምሮበታል። በመጨረሻ በመርሀ ግብር መሪው በዶ/ር ብርሃኑ ተሾመ በዓለም ላይ ያሉ ኢትዮጵያዊያን መጽሐፉን በ www.Ethioamharic.com ድረ ገጽ ማግኘት እንደሚችሉ ገልጸው መርሀ ግብሩ ተጠናቋል።